Kanton St.Gallen
Gesundheitsdepartement

Wir machen das. ST.GALLEN IMPFT!



# የኮቪድ ክትባት

## አሁን ይመዝገቡ

## www.wir-impfen.ch

በቅዱስ Gallen ካንቶን ውስጥ ያሉ ጎልማሶች በሙሉ በነጻ ለሚሰጥ የኮሮና ክትባት ሊመዘገቡ ይችላሉ።





## ምዝገባ በክትባት ማዕከል ውስጥ

በክትባት ማዕከል ውስጥ ለክትባት ቀጠሮ እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል፡፡
በይነመረብ፣ የኢሜል አድራሻ ከሌለዎት ወይም የቋንቋ ችግር ከገጠመዎት፣
ሌሎች ሰዎችን ለዕርዳት ይጠይቁ (ቤተሰብ፣ ጓደኞች ወይም የምያውቋቸውን ሰዎች)፡፡

1. ድህረገፅ www.wir-impfen.ch ይጎብኙ
2. «Zur Registrierung» የሚለውን ጠቅ ያድርጉ
3. መመዝገብ: የመጀመሪያ እና የአባት ስም፣ የኢሜል አድራሻ እና የይለፍ ቃል ያስገቡ፣ ከዚያ «Registrieren» የሚለው ላይ ጠቅ ያድርጉ።.
4. ምዝገባዎን የሚያረጋግጡበት ኢሜል ይደርስዎታል፡፡
5. ከምዝገባ በኋላ ለክትባት ቀጠሮ መመዝገብ ይችላሉ፡፡ የምፈለጉተን የክትባት ማዕከል ይምረጡ (ቅዱስ Gallen፣ Wil፣ Rapperswil-Jona ወይም Buchs) እና የምዝገባ ቅጹን ይሙሉ።
6. የምዝገባ ማረጋገጫ በኢሜል ይደርስዎታል፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እርስዎ ለኮቪድ 19 ክትባት ተመዝግበዋል። የክትባቱን ቀጠሮ በኢሜል ያገኛሉ። የመጀመሪያው ቀጠሮ የማይመች ከሆነ፣ ሌላ ቀጠሮ መምረጥ ይችላሉ፡፡

## ምዝገባ የቤት ሐኪም ዘንድ

የቤት ሐኪም ዘንድም ልመዘገቡ ይችላሉ፡፡
ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሰዎች የቤት ሐኪም ዘንድ ብቻ ነው የሚከተቡት፡

- ለመድኃኒቶች ወይም ለክትባቶች ከባድ አለርጂዎች ያላቸው ሰዎች
- ሥር የሰደዱ በሽታዎች ያለባቸው ሰዎች
- የክትባት ምክር የሚፈልጉ ሰዎች
- ነፍሰጡሮች

## ተጭማሪ መረጃዎች

ቀደም ሲል ኮሮና ነበረዎት? እንደዚያ ከሆነ እርስዎ ቢያንስ ለ6 ወራት መከላከያ አለዎት፤ ስለዚህ ክትባቱን 6 ወራት መጠበቅ ይችላሉ፡፡

## ክትባትን በተመለከተ ጥያቄ አለዎት?


የስልክ መሥመር / ስልክ ቁጥር: 058 229 22 33
support@wir-impfen.ch


